
# ሕብረ ቅላጼ

ወገናዊነት ለምንጩ

# ሕብራዊነት ሲመረመር


## ቃ ል፤

ሃሳቡ፣ ማለትም ምንጩ ፣ ሰላምና ፍጹማዊነትን በሰፊው ያቀርባል፤ የማይጨበጠውና የማይገረሰሰው የወድያኛው ዓለም በእርግጠኝነት በነዚህ የተሞላ መሆን ሰለአለበት።


VI.
ሁለንተናዊ
I.
ማህበራዊ
ምሕረት
III.
ቁስ፥ አካላዊ
ቤተ፥ሰላም
ዕውቀት
ነጻነት
ጥበብ
II.
ባህላዊ
ተስፋ፥ብርሃን
IV.
መንፈሳዊ
V.
የሰው ልጅ


# አንዱ ምንጬ

*ለኢትዮጵያ ሃገራችን ደህንነት*


S
I
SIDE
E
D


# አንዱ ምንጭ

**ሰላምና ፍጹማዊነትን በሰፊው ያቀርባል፤ የማይጨበጠውና የማይገረሰሰው የወድያኛው ዓለም በእርግጠኝነት በነዚህ የተሞላ መሆን ሰለአለበት።**




*ሰላምና ፍጹማዊነት* ግን የሰማይ መና ሳይሆኑ በታሪክና በምርምር የሚኮተኮቱ መድረሻ ግቦች ናቸው። የሰው ልጅ ከፍ ያለው ***መድረሻ፥ዓላማውን*** ተከኖ ከ**ምንጩ** ጋር ይገናኝ ዘንድ።

የሰው ልጅ የአራቱን ሕብረ፥ዜማ /ሰላምና ፍጹማዊነት፤ ባህልና ዕምነትን/ የሚቀላቀለው የባህልና የዕምነት ግቦች ባለቤትና ባለጉዳይ በመሆን፣ እነዚህን ወደ ፍጹማዊነት ለማድረስ በጊዜናቦታ እየገሰገሰና ባህላዊ እድገትን ሲያስመዘግብ ነው።




*„መልካም ነገሮች ሁሌ ሶስት ሶስት እየሆኑ ነው የሚመጡት“ ይባላል*

# ማህበራዊ መስክ

ሰላም ለሰው ልጅ፣ እንደ ማሳረጊያ ብርቅ ጉዳይ ተዋቅራ የምትከበበው

በ *ስነ፥መንግሥት፣ በማህበረ፥ሰብ ና በቤተ፥ሰብ* ማእከል ውስጥ ነው።




## ማህበራዊ መስክ

***የሰነ፥መንግሥት፣ የማህበረ፥ሰብና የቤተ፥ሰብ*** መስተጋብር ሰላምን ከፍ ባለው ***ቤተ፥ሰላም*** አያዋቀረ የሚየቀርብልን **የታሪክ እርምጃ** ነው።

*


# ሰብዓዊ መስክና ሁለንተናዊ መስክ

***ቤተ፥ሰላም*** ተብሎ የተሰየመው ፍሬ ነገር፣ የሕብረ፥ቅላጼው ማዕከል፣ ወይንም የፈጣሪነት አስኳሉ ***የመጀመሪያው የሚቀያየር መለያው*** (variable) ሲሆን፤ ይህም፣ የሰው ልጅ የተስፋ ፍንጣቂ ነጸብራቅ በሆነው፣ በመንፈሳዊ የምሕረት ግንኙነት ተወሳሰቦ የተዘረጋ ነው።

ቤተ፥ሰላም ማለት ዕውቀትና ርቀት፣ጥበብና ነጻነት ገንኖ የሚገኝበት፣ በሃሳብ የሚታለም፣ ከፍ ያለ የሰው ልጅ ማህበራዊ የሰላም ሰፈር ነው።

- ከፍ ብሎ የሚታሰብ፣ መንፈሳዊ ተፈጥሮ ያለው ማህበራዊ ና ነጻ ክልል !

# መንፈሳዊ ምሕረት





# ሰብዓዊ ተስፋ

*

# ቁስ፥አካላዊ መስክ

መድረሻው ሃብት የሚሆነው ፍጹማዊነት እየረቀቀ፣ የፈጣሪነት ችሎታ የሚዳብረው፣ ምንጩ በሰው ልጅ እራሱን ሲከስት ነው። ምርምርና ሳይንስ እየገሰገሰ ሲራመድ፣ በ*ሰው፣ በፍጥረትና በሰማያት* ጉዳዮች ላይ የሚከናወነው የረቀቀ ጥናት ወደ ማሳረጊያው **የዕውቀት** ማዕከል እያደረሰ ይመጣል። *ዕውቀትም* የፈጣሪነት ማዕከሉ ***ሁለተኛው የሚቀያየር መለያው*** ነው።





ቁስ፥አካላዊ መስክ

*

# ባህላዊው መስክ

ባህል የሰው ልጅ የሰላማዊ ሕብረ ግንኙነት መሰረት ሲሆን፣ ይህም የሚከሰተው በስነ መንግሥት
***ህግና ደንቦች***፣ በማህበረሰቡ ***ስነ ምግባርና በቤተ፥ሰባዊ የፍቅር መሰረት*** ነው።
በሰው ልጅ ሰብዓዊ ባህል ዕድገት አማካይነት፣ ***ነጻነት*** ላይ ይደረሳል፣
***ነጻነትም*** ፣ የፈጣሪነት ማዕከሉ ውስጥ ***ሶስተኛው የሚቀያየር መለያው*** ነው።





ባህላዊው መስክ

*

# መንፈሳዊ መስክ

ዕምነት ከፍጹማዊነት ሃብት ጋር እጅ ለእጅ የሚደጋገፍ፣ የፈጣሪነት ቀስቃሽ ክስተት ነው።
***እምነት፣ ሃይማኖትና ህሊና*** በቤተ፥ሰላም ክልል ውስጥ እርስ በርሳቸው ሲስተጋበሩ፣
ለሰው ልጅ የዕምነት ግቡን ያበጁለታል። ይህ ግብ ጥበባዊነት ሲሆን፤
***ጥበብም*** የፈጣሪነቱ ማዕከል ውስጥ፣ ***አራተኛው የሚቀያየር መለያ ው*** ይሆናል።




መንፈሳዊው መስክ

*

***ተሰፋ ለሰው ልጅ፣*** **የሕይወቱ መርህ የሚሆነውን ያህል፣** ለፈጣሪነት ማዕከሉም ***<u>አምስተኛው ተቀያያሪ</u>*** ***<u>መለያው</u>*** ነው። ይህም ***ምንጬ*** ለሰው ልጅ የሚያስመለክተው ***መድረሻ፥ግቡ፤ ማለትም፣***
የሕይወት ስረ፥መንስኤው እንዳለ ሆኖ ነው።

በሕይወት ውስጥ አንዳችም ጉዳይና ነገር፤

# በሕብረ ቅላጼ(1

ውስጥ የማይጠቃለል የለም።

ባጭሩ፥

I. – **ሰላም** እንደ ሚደረስ ግብና ድንበር፤ ወይንም፣ **ቤተ፥ሰላም ማዕከሉ** ውስጥ የሚታለም ጉዳይ ሆኖ ሳለ፣ ስነ **መንግሥት፣ ማህበረ ሰብ፤እና ቤተ፥ሰብ** **የማህበራዊ መስኩን** መዋቅራዊ ተፈጥሮ ያበጃሉ።

II. – **ባህል** እየተኮተኮተ የሚያድግ ዳር ድንበር፤ ወይንም **ነጻነት ማዕከሉ** ዘንድ ሊደረስበት የሚቻል ክስተት ሲሆን፤ **ሕገመንግሥት፣ ግብረ ፥ገብ እና ፍቅር** የሰው ልጅ ንቁ **የባህል መስኩን** ይገልጻሉ። እነዚህ **ማህበራዊ ና ባህላዊ መስኮች ስነ፥ አይምሮን** (intelligence) **የሰው ልጅ ለሆነው ከፊል፥ዓለም፣ እንደ ዋነኛው የማዕከሉ ምሰሶና ተፈላጊ** (attractor) **ቁም ነገር አድርገው ያቀርቡለታል።**

III. – **ሀብት፣** ፈጠሪነትን ፍጹም ለማድረግ ሊደረስበት የሚቻል ዳርድንበር ሲሆን፤ ወይንም **ዕውቀት፣ ማዕከሉ** ዘንድ ፍጹማዊነት እንዲያገኝ፣ **ሰማያት** (universe) **ተፈጥሮና የሰው፥ዘር የቁስ፥ አካላዊው መስክ** ዋነኛ የጥናት ሰረ መሰረት ይሆናሉ።

IV. – **ዕምነት** እንደ ሰው ልጅ መድረሻ ግብ / ዳር ድንበር፤ ወይንም **ጥበብ በማዕከሉ** ዘንድ ታልሞ ተመርምሮ ሊደረስበት የሚቻል ሲሆን፤ **እምነት ሃይማኖትና ሕሊና** ሲዛመድ፣ የሰው ልጅ የንቃት ሃያልነት **በመንፈሳዊ መስክ** ተጠቅልሎ ይታያል። **ቁስ፥አካላዊ ና መንፈሳዊ መስኮቹ ስነ፥ሀይልን** (energy) **እንደ መሠረታዊ ተፈላጊ ቁም ነገርና ለአምላካዊው /ከሰውልጅ ለተለየው/ ከፊል ዓለም፣ እንደ ዋነኛው ምሰሶ አድርገው ያዛምዱታል።**

V. – **አምስተኛው፣** የሰው ልጅ መለኮታዊው (transcendental) መስክ **መድረሻ፥ግቡ** ና አንድ ምንጬ ላይ ለመድረስ፣ ተሰፋ፥ብርሃንን የሕይወቱ መርህ አድርጎ ሲደክም፣ በሁሉም ረድፍ ከአራቱም መስኮች ጋር እየተዋሃደ ይስተጋበራል። ማለትም፣የሰው ልጅ፣ በማህበራዊው፣ በቁስ፥አካላዊው፣ በባህላዊው እና እንዲሁም በመንፈሳዊው መስኮች ውስጥ ሁሉ ይስተጋበራል፣የስተናገዳል ማለት ነው።

VI. - **ስድስተኛው፣** መለኮታዊው የሁለንተናዊነት /የእግዚአ፥ብሄር/ መስክ፣ **አንዱ ምንጭ** የመጨረሻውን የመሃሪነት መርሁን የሰውን ልጅ ለማዳን አንግቦ፣ ባሉት ረድፎች በሙሉ፣ ከሁሉም፣ከአምስቱም መስኮች ጋር፣ በሰው ልጅ መለኮታዊው መስክ አማካይነት ይስተጋበራል። ማለትም፣ የሁለንተናዊነት /የእግዚአ፥ብሄር/ መስኩ፣ ከሰውልጅ መለኮታዊው መስክ ጋር እየተስተጋበረ በውስጣው ግንኙነት ይዘማመደዋል ማለት ነው።

# የሚፈለጉት ቁም፥ነገሮች(ግብ)

(Attractors of Meanings)

በሕብረ፥ቅላጼው መድረኮች ውስጥ ያሉት እያንዳንዳቸው፣ ንዑስ፥ክፍሎች የየራሳቸው

ተፈላጊ ቁም፥ነገር አለቸው። እነዚህም የሰው ልጅ የሚከተላቸው ከፍ ያሉ ግቦቹ (ግብ) ናቸው።

## I. ማህበራዊው መስክ

የህዝብ አገዛዝ
ብልጽግና
ማህበራዊ ሀብት

## II. ባህላዊው መስክ

ለህግ መገዛት (የህግ በላይነት)
ማህበራዊ ፍትህ
ልቦና

## III. ቁስ፥አካላዊው መስክ


ሰው መሆን፤ ሰብዓዊ ነት
ንቃተ ፥ሕይወት
የፍጥረት ምንጭና ምስጢረ፥ፍጥረት

## IV. መንፈሳዊው መስክ

ንቃተ፥ህሊና
የዕውነት ፍለጋ/ምስጢረ፥ስላሴ
ቁም፥ነገር ና ራዕይ

# I. የማህበራዊው መስከ ነውስ ክፍሎች(ግብ)

## 1. ስነ፥መንግሥት





1. ሕግ ፥አውጪ ጉባኤ
2. ሕግ፥አስፈጻሚ አካል
3. ሕግ፥መወሰኛ አካል

**4. የህዝብ አገዛዝ**

*

## 2. ማህበረ፥ሰብ





1. ትምህርት
2. ምርት
3. ስርጭትና ማህበራዊ ገቢያ

**4. ብልጽግና**

*

### 3. ቤተ፥ሰብ




1. ሰብአዊ ስነ፥አይምሮ

2. የሥራ ሃይልና አገልግሎት


3. ገቢ ና ፍላጎት

**4. ማህበራዊ ሀብት**

***

## II. የባህላዊው መስከ ንዑስ ክፍሎች (ግብ)

### 1. ሕግ




1. ሰብዓዊ መሠረታዊ ህግ


2. ፍትሃ፥ብሄርና የተዛመዱ ህጎሽ

3. ወንጀለኝ መቅጫና የተዛመዱ ህጎች

**4. ለህግ መገዛት (የህግ በላይነት)**

*


## 2. ስነ፥ምግባር




1. ማህበራዊ
2. ባህላዊ
3. ተለምዶ፥ታሪካዊ
4. ማህበራዊ ፍትህ

*

## 3. ሰብዓዊ ፍቅር





1. መንፈሳዊ
2. አካላዊ
3. ባህላዊ
4. ልቦና

***

## *III.* የቁስ፥አካላዊው መስከ ንዑስ ክፍሎች (ግብ)


### 1. የሰው፥ዘር




1. ሰብዓዊ ስነ፥አፈጣጠር ና የተዛመደ ዕውቀት
2. ስነ ሰብዓዊ ዘር ማንዘር ና የተዛመደ ዕውቀት
3. ስነ ሰብዓዊ ሕይወት ና የተዛመደ ዕውቀት
4. ሰው መሆን፤ ሰብዓዊነት

*


### 2. ስነ፥ፍ ጥ ረ ት




1. ስነ ክልለ፥ተፈጥሮ ና የተዛመደ ዕውቀት
2. መልክዓ ምድር ና የተዛመደ ዕውቀት
3. መልክዓ ማድን ና የተዛመደ ዕውቀት
4. ንቃዓተ፥ሕይወት

*

### 3. ሰ ማ ያ ት





1. ሰና መሠረታዊ አፈጣጠር ና የተዛመደ ዕውቀት
2. ኮከበ፥ ምርመራ ና የተዛመደ ዕውቀት
3. የስነ፥ሰማያት ምርምር ና የተዛመደ ዕውቀት
4. **የፍጥረት ምንጭና ምስጢረ፥ፍጥረት**

***

## IV. የመንፈሳዊው መስክ ንዑስ ክፍሎች(ግብ)


### 1. ህ ሊ ና




1. ሰብዓዊ
2. ግላዊ
3. ማህበራዊ
4. **ንቃተ፥ህሊና**

*

## 2. ሃይማኖት





1. ስነ፥ፍልስፍናዊ
2. ሃይማኖታዊ
3. ባህላዊ

**4. ዕውነት ፍለጋ/ምስጢረ፥ፍጥረት**

*

## 3. ዕ ም ነ ት




1. ብርሃነ፥ዕውቀት
2. ሰነ ፍልስፍናዊ ዕምነት
3. ምሁራዊ ዕምነት

**4. ራዕይ ና የሕይወት ፍሬ፥ነገር**

***

# ሁሉም ቁም ነገር ሲሰበሰብ

በህዝብ አንደበት፣ ***„መልካም ነገሮች ሁሌ ሶስት ሶስት እየሆኑ ነው የሚመጡት"*** ይባላል። በየመስኩ *ያሉት ሶስት ሶስት* ግቦች ደግም ባንድነት እየተቀላጠፉና እየተቀማመሩ *ከፍ ያለ መልካም ነገር* ይወጣቸዋል። (የሕይወት „ምስጢረ፥ስላሴው" ሲገለጥ!)

## አንደኛ፣ *ለሰላም*




1. ***የህዝብ አገዛዝ***
2. ***ብልጽግና***
3. ***ማህበራዊ ሀብት***

## ሁለተኛ፣ *ለሰብዓዊ ባህል*




1. ***ለህግ መገዛት (የህግ በላይነት)***
2. ***ማህበራው ፍትህ***
3. ***ልቦና***

## ሶስተኛ፣ *ለፍጹማዊነት/ ሃብት*




1. ***ሰው መሆን፤ ሰብዓዊነት***
2. ***ንቃተ፥ሕይወት***
3. ***የፍጥረት ምንጭና ምስጢረ፥ፍጥረት***

## አራተኛ፣ ለዕምነት




1. ***ንቃተ፥ህሊና***
2. ***የዕውነት ፍለጋ/ምስጢረ፥ፍጥረት***
3. ***ራዕይና የሕይወት ፍሬ ነገር***

አዎ! እነዚህ ሁሉንም ሰው የሚያምሩና የሚስቡ ዝርዝር ቁም ነገሮች፣ ማለትም ከፍ ያሉ ግቦች ፣

**በመላው የሰው ልጅ የሚታለሙ ትላልቅ ዓላማዎች፣**
**በህብረ፥ቅላጼው አራት ከፍተኛ ግቦች፣ ተጠቃለውና ተጠራቅመው የሚገኙት ናቸው።**

**አንደኛ፣**

# ሰ ላ ም

**ሁለተኛ፣**

# ሰ ብ ዓ ዊ  ባ ህ ል

**ሶስተኛ፣**


# ፍ ጹ ማ ዊ ነ ት

**አራተኛ፣**

# ዕ ም ነ ት

*

የሰው፥ልጅ ተስፋ፥ብርሃኑ ከቀረበውና የሁለንተናዊው ፈቃደ፥ምሕረት ከተጨመረበት ደግሞ
ሕይወት ዞራ ከምንጩ ዘንድ እየገጠመች ነው፣ ለማለት ይቻላል።
የሰው፥ልጅ ራዕዩ፣ መድረሻ ግቡ ነው።


VI.
ሁለንተናዊ
I.
ማህበራዊ
ሰላም
ምሕረት
III.
ቁስ፥ አካላዊ
ፍጹማዊነት
ቤተ፥ሰላም
ዕውቀት
ነጻነት
ጥበብ
II.
ባህላዊ
ሰብዓዊ
ባህል
ተስፋ፥ብርሃን
IV.
መንፈሳዊ
ዕምነት
V.
የሰው ልጅ

# ሕብረ፥ቅላጼ

## <u>የሕይወት ትርጉሙ / ፍሬ፥ነገሩ</u>

### ሕይወት ማለት፣

የእግዚአብሄርን፣ ማለትም የፈጣሪነትን ብቃት፣ በሁሉም የተፈጥሮ ጉዳይ ውስጥ እየቀሰቀሰ፣ሰብዓዊ፣ ሁለንተናዊ ና የሰው፥ዘር ኪነ፥ውበታዊ ተፈጥሮን የሚያድስ፣ አያሌ ዘርፍ ያለው የተወሳሰበ የተፈጥሮ ሂደት ነው። የዚህም ማሳረጊያ ግቡ፣ብዙ ትውልድን እያሸጋገረ በህብራዊነት የሚካነውን የሰው ልጅ መፍጠር ነው።/1

የሕይወት ፍሬ ነገር የሚገኘው፣

**1ኛ፣ በማህበራዊ መስክ**

**2ኛ፣ በባህላዊ መስክ**

**3ኛ፣ በቁስ፥አካላዊ መስክ**

**4ኛ፣ በመንፈሳዊ መስክ**

ውስጥ ሲሆን፤ እነዚህን የሚያዋስኑ መለኮታዊ ድንበሮች ደግም  አሉ፥

ከእነዚህ መስኮች አብራክ ወጥቶ የሚከሰተው፣
**5ኛ፣ የሰው፣ ልጅ መስክ እና**

ከሁሉም መስኮች ጋር ተዛምዶ የሚስተጋበረው፣
**6ኛ፣  ሁለንተናዊ መስክ።**

*(መስኮች፣ በሚያያዙ ማስተሳሰሪያዎች ይቀላጠፋሉ (Planes: "the conjunctive syntheses"/2))*

ለእነዚህ መስኮች፣ እንደ ጀርባ ምሶሶ ሆነው የሚቆሙና የሚያገለግሉ ስምንት አድማሶች ወይንም መለኪያውች አሉ።
*( አድማሶች፣ በሚያያይዙ ማስተሳሰሪያዎች ይቀላጠፋሉ፣(Dimensions: "the connective syntheses"/2))*

**1ኛ፣  ስነ፥መንግሥትና ሕግ**

**2ኛ፣  ማህበረሰብ ና ስነ፣ምግባር**

**3 ኛ፣ ቤተሰብና  ፍቅር**

**4ኛ፣ የሰው፥ልጅ ና ተስፋ፥ብርሃኑ**

**5ኛ፣ የሰው፥ዘርና ሕሊና**

**6ኛ፣ ስነ፥ፍጥረትና  ሃይማኖት**

**7ኛ፣ ሰማያታትና ዕምነት**

**8ኛ፣ እግዚአብሄር/ ሁለንተናዊነት ና ምሕረት**

በነዚህ አድማሳት መሃከል አያሌ የሚያወራረሱና  የሚያጠላለፉ አገናኝ ከፍሎች ሲኖሩ፣ እየተቀባበሉ እርስበርስ የሚያነቃቁ መስተጋብሮችም አሉ።
*(ተወራራሽ ፥ ከፍሎች፣ በሚስተያዩ/ በሚመዛዘኑ ማስተሳሰሪያዎች ይቀላጠፋሉ፣(Cross-sections: reflective syntheses))*

እነዚህ አድማሶች የየራሳቸው ማዕከላዊ ምሶሶ / የሚስቡ፣ የሚወደዱ ልዩ ቁም ነገሮች/ አሏቸው።
*(ማዕካላዊ ምሶሶዎች፣ በሚያለያዩ ማስተሳሰሪያዎች ይቀላጠፋሉ፣(Axes: “the disjunctive Syntheses” /2))*

**1ኛ፣ ሰብዓዊነት (ሰ)**

**2ኛ፣ ስነ፥አይምሮ/ ንቃተ፥ሕሊና (ሕ)**

**3ኛ፣ ኪነት (ኪ)**

**4ኛ፣ መድረሻ፥ግብ (ግ)**

**5ኛ፣ ቁሳቁስ (ቁ/m)**

**6ኛ፣ ስነ፥ሃይል (ሃ/E)**

**7ኛ፣ ብርሃን (ብ/c)**

**8ኛ፣ ምንጬ (ም)**

***ተመራማሪው አይንስታይን ስለ ስነ፥ሃይል፣ብርሃንና ቁሳቁስ ያገኘውን ማመዛዘኛ/ ፎርሙላ/፣ ባንድ በኩል፣ (በእግዚአብሄሩ ከፊለ፥ዓለም ውስጥ ብለን ለምንሰይመው) ለቁስ፥አካላዊውና ለመንፈሳዊው መስኮች ማመላከቻ አድርገን ብንወስደው፤***

*E=mc2 ; Energy = Mass x (Speed of Light)2*
***ቁሳቁስ፣በብርሃን ፍጥነት እጥፍ ጊዜ ቢባዛ፤ ስነ፥ሃይል ን ያከላል ብሎ መመዘን ይቻላል ማለት ነው።***
***ሃ = ቁ *ብ *ብ***

***በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ለማህበራዊው ስነ፥ፍጥረ ት መገንዘቢያ ይሆን ዘንድ ፣ (የሰው፥ልጅ ሌላው ከፊለ፥ ዓለም ብለን በምንጠራው) ለማህበራዊውና ለባህላዊው መስኮች፣ ተመሳሳይ ማመዛዘኛ ማስቀመጥ ይቻል ይሆናል።***

*I= hq2 ; Intelligence = Humanity x (Quality of Music)2*
***አንድ የሆነ፣ ሰብዓዊ የህሊና፥መመዘኛ (ሰ)፣ በስነ፥ ኪነት ረቂቅነት(ኪ) እጥፍ ጊዜ ቢባዛ ወይንም ቢገናኝ፤ ለስነ፥አይምሮ (ሕ) ከብርና ክብደት ማለካኪያ ይሆን ይሆናል ለማለት ነው።***
***ሕ = ሰ* ኪ* ኪ***

በዚህ የአመለካከት ዘይቤ/ (model/ሞዴል)፣ የሕይወት ትርጉሙ፣
በአራቱ መስኮች መሃከልና በየራሳቸው በየመስኮዎቹ ውስጥ ***ሕብራዊነትን/ ሕብረ፥ቅላጼን*** እያስተናገዱ፣ በየመስክ፥ዘርፉ ያሉት ከፍተኛ የሰው ልጅ ዓላማዎች ላይ መድረስ ነው።

እነዚህም፥


# **ሰላም፣ ሰብዓዊ ባህል፣ ፍጹማዊነት**/ሃብት እና፣ **ዕምነት**

ናቸው።


እነዚህ ዓላማዎች የሚሳኩትን ያህል፣ ሕብረ፥ቅላጼውም፣ መለኮታዊው የሰው ልጅ ላይ፥ ማለትም **መድረሻ፥ግቡ** ላይ ደርሶ፣ **ከምንጬ** ጋር ለመግጠም ዝግጁ እንዲሆን ያደርገዋል። ዛሬ ያለንበት ዘመን ግን፣ አሳዛኝና እንዳውም፣ ጭራሹኑ፣ በፀረ፣ሕብራዊነቱ የተሞላ ነው። ይህ የዛሬው ዘመን የሚያሳዝን የሆነው፣ ፀረ፣ሕብራዊነቱ፣ በሕይወት መስኮቹ መሃከልም ሆነ በራሳቸው በየመስኮዎቹ ውስጥም ስለገነነ ነው።

****


*1).Reformulated after an encounter with .complexity theory…and further philosophical survey (cf. Original intuition, 1/2006).*
*2) .Connective, conjunctive and disjunctive syntheses. Concepts from Kant, whitehead and Deleuze, as interpreted by Steven Shaviro, http://www.shaviro.com; and my fourth one, what I call reflective syntheses*



The Cycle of
Divine Proportion
Harmony
Dimensions
1. State
2. Community
3. Family
Social Sphere
h
LIGHT
Source
The Absolute
The Cycle of
Divine Proportion
Harmony
Dimensions
5. Mankind
6. Nature
7. Universe
Material Sphere
m
Science
Science
History
Peace
Wealth
Space
Beyond
I-ntelligence
E-nergy
Beyond
I=hq²
E=mc²
History
Culture
Faith
Space
4. The Human
Destiny
Culture
Culture
q
c
Cultural Sphere
1. Laws
2. Ethics
3. Love
Divine Proportion
Harmony
Dimensions
The Cycle of
BE-ING
(Dasein)
Spiritual Sphere
5. Conscience
6. Religion
7. Faith
Harmony
Divine Proportion
Dimensions
The Cycle of



VI.
Absolute
I.
Social
Deliverance
III.
Material
Heaven
Knowledge
Freedom
Wisdom
II.
Cultural
Hope
IV.
Spiritual
V.
Human

# HARMONY





$I = hq^2$ $E=mc^2$

Source <<== >>> Funktion (I, E) <<== S I D E ==>> Funktion (E, I) <<==>>> Destiny



# ሕብረ ቅላጼ(1

1) *ሕብረ ቅላጼ፣ የአማርኛ የቋንቋ ሊቃውንት ይቅርታ ያድርጉልኝና ሕብረ ቅላጼ የሚለውንም ሆነ አንዳንድ እዚህ ለትርጉም የተገለገልኩባቸው ቃለቶች የተወሰዱትና እየተጣመሩ ለእንግሊዝኛው የተተኩት፣ መንፈሱን የታሻለ ያንጸባርቃሉ ብሎ በማሰብ ነው። ለምሳሌ፣ ሕብረ፥ቅላጼ የተወሰደው መቀለስ ከሚለው ግስ ወደ ቅላሴ፣ከዚያም ቅላጼ ተብሎ፤ ብዙ ነገሮች በህብረት ሲቀልሱ ወደ አንዱ ህብራዊነት ማምራቱ ና ሕብረ ቅላጼ መባሉ፣ HARMONY የሚባለውን የተሻለ አሚልቶ ይተካዋል በማለት ነው።*



*ለኢትዮጵያ ሃገራችን ደህንነት*